# የመለስ ቡድን አጥፊነትና የሌሎች
# አቋም- እስካሁን ካየሁት ባጭሩ

ከአገር ወዳድ ተቆርቋሪ
ጃንዋሪ 18፤ 2010

**ከኢትዮሚድያ አዘጋጅ** - መለስ ዜናዊ እና በሱ ዙርያ የተኮለኮሉት ባለስልጣናት በትግራይ ህዝብ አይን እንደጠላት በሚታዩበት ውቅት ትግራይን ከኢትዮጵያ አስገንጥለው ሪፑብሊክ ሊመሰርቱ ነው ብሎ ዘገባ ማቅረብ አሁን ትግራይ ውስጥ ካለው ሁኔታ ፈጽሞ የማይጣጣም ነው። የትግራይ ህዝብ ጥያቄ አገራችን መቼ ነው ቀይ-ባህርን የምታስመልሰው? ኧረ ለመሆኑ መቼ ነው ኢትዮጵያዊ መንግስት የሚኖረን? የሚሉ ጥያቄዎች እንጂ "ኧረ መቼ ነው የምትገነጥሉን?" የሚል እንዳልሆነ በቅርቡ በክልሉ ሕዝባዊ ስብሰባ ካደረጉት የመኢአድ እና የዓረና ትግራይ አመራር አባላት ጠይቆ መረዳት ይቻላል። የመለስ ዜናዊ ፍጻሜ ከኢትዮጵያ ስልጣን መልቀቅ ጋር አብሮ የሚያከትም እንጂ ሰውየው ሌላ የትግል ሀሁ ለመጀመር ወደ መቀሌ የሚጓዝበት ምንም ዕድል እንደማይኖር ጉዳዩን በቅርበት እና በጥልቀት የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን በየጊዜው ሲያስረዱ ቆይተዋል። ይልቁንስ በግንጠላው ወጥመድ ዘው ብለን ገብተን እንድንሸነቀር የመለስ ዜናዊ ዓላማ መሆኑን መረዳት ይበጃል። የጸሀፊው ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት በማክበር ጽሁፋቸውን ከምስጋና ጋር ለንባብ አቅርበናል።

= = = = = // = = = = // = = = = =

ሰግብግቡና ጠባቡ የመለሰ ቡድን በብልጣብልጥነት ስልጣን ከያዘ ዕነሆ አሁን አሰራ ዘጠኝ አመት ሊሆን ነው። አንዳንዴ ከምስነዝረው ይፋ ተቃውሞ በሰተቀር ከሞላ-ጎደል በታዛቢነት ቡድኑ የሚሰራውን ጥፋት በቁጭት ስመለከት ቆይቻለሁ። እራሳቸውን በተቃዋሚነት መድበው ያሉትንም በማነጻጸር ተመልክቻቸዋለሁ። እስካሁን ካየሁት ባጭሩ ቀጥሎ ከገለጽኳቸው ድምዳሚዎች ላይ ለመድረሰ ችያለሁ። ምናልባት ተሳስቼ እንደሆነ ወይም የጎደለ ካለም ሌሎች ቢያርሙኝ ወይም ቢጨምሩበት ለመማር ይበጃል።

<u>የመለሰ ቡድን አጥፊነት</u>

- የመለሰ ቡድን ትግራይን ለመገንጠል ብሎ የተነሳበትን አላማ ሙሉ በሙሉ ያየካሂያደ ያለ አጥፊ ቡድን ነው። ማሳመኛዎች:-

  - ቡድኑ የታቀፈበት የድርጅት ሰም መገንጠልን የሚያመለክት ነው
  - በድርጅቱ ፐርግራም ላይ መንገጠልን በግልጽ አሰፍሮታል
  - ኢትዮጵያን በመሪነት አሰተዳድራለሁ የሚል ቢሆንም፤ የመገንጠሉን አላማ እሰካሁን አልቀየረም፤ እንዲያውም ሌሎች ብሄረሰቦች ይህንን አላማ እንዲከተሉ በህግ በማጽደቅ ይገፋፋል
  - ከቡድኑ ጋር አብረው ይሰሩ የነበሩ የቀድሞ ጓዶች የቡድኑን የመገንጠል አላማ በይፋ አረጋግጠዋል፤ እያረጋገጡም ነው
  - የትግራይ ክፍለ ሃገርን ከሌሎች ቦታዎች ለይቶ በአገር ደርጃ (ማለት፡ በጦር ሀይል፤ በኢኮኖሚ፣ በንግድ፤ በፖለቲካ፤ ግዛት በማስፋፋት፤ በሰነ ልቦና ወዘተ) በማሳድግ ለግንጠላ ዕያመቻቸ ነው
  - የትግራይ ተውላጅ የሆኑ የሚደግፉትን ኢትዮጵያውያን ለይቶ በመጥቀም (ማለት፡ በሰልጠና/በትምህርት፤ በኢኮኖሚ፤ መሰልጣን ወዘተ) ለአዲስ አገር ምስረታ ዕያዘጋጀ ነው
  - ግንጠላውን ሊያከሽፉ ይችላሉ የሚላቸውን ሁሉ በተቻለው መጠን ያዳከማል፤ ያጠፋልም
  - በተለይ ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ያጠቃል፤ ለማጥፋትም የሚችለውን ያደርጋል

- የመለሰ ቡድን ኢትዮጵያንና ህዝቧን የሚጠላ ቡድን ነው

  - ሰለሆነም እላይ እንደተዘረዘረው የራሴ የሚለውን የአግሪቱን አካል ገንጥሎ ለመለየት በእቅድ ተገቶ ይሰራል
  - ህዝብ የመረጣቸውን መሪዎች አሰሮ፤ አባሮና ገድሎ ከህግ ውጪ በስልጣን ላይ ተቀምጧል

- በአገሪቱ ህዝቦች መካከል የተለያዩ ቅራኔዎችን በመፍጠር የዜጎችንና የአገሪቱን አንድነትም ሆነ ጥንካሬ አዳክሟል
- የአገር አካል የሆኑ ህዝቦችንና መሬት በገዛ ፈቃዱ እንዲገነጠሉ አድርጓል
- የአገሪቷን መሬት በገዛ ፈቃዱ ለውጭ አገር አሳልፎ ሰጥቷል
- የአገሪቷን ንብረት ሁሉ በራሱ ወይም በጥቂት ደጋፊዎቹ ቁጥጥሩ ስር አድርጓል
- የሚጠላዉን ህዝብ መሬት አልባ በማድረግ የአገሪቷን መሬት በሙሉ ይቆጣጠራል
- የአገሪቷን ለም መሬት ለዉጭ አገር ዜጎች (እንደጠላት የሚያይዋትንም ጨምሮ) በማከራየት ክፍያውን ለግሉ ጥቅም ያዉላል
- ለህዝብ የፖለቲካ ነጻነት ሙሉ በሙሉ ከልክሏል
- የሚጠላዉን ህዝብ በድህነት፤ በበሽታ፤ በርሃብ፤ በእስራት በሰፊው ከህግ ውጪ ይቀጣል
- የአገሪቷ ጠላት ከሆኑ አገሮች ጋር አብሯል
- የአገሪቷን ህዝብ ጥቅም ለውጩ አገሮች/ዜጎች አሳልፎ በብዙ መንገድ ሰጥቷል
- የአገሪቷ ህዝብ ከጎረቤት አገር ህዝቦች ጋር እንዲጋጭ ይጠራል

<u>የውጭ አገሮች/ሰዎች ለመልሰ ቡድን የሚሰጡት ድጋፍ</u>

- ቡድኑ ድጋፋቸውን አግኝቶ እስከተቻለው ድረስ በሰልጣን ለመቆየት (ማለት፤ ከመገንጠሉ በፊት) የውጭ አግሮችን ጥቅም እንደሚፈልጉት በመጠበቀ የሚፈልገውን ድጋፍ ብዙዎች ያገኛል። የህንንም የሚያደርገው የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም በመጻረር ነው፡፡ ይህንን አሰመልክቶ አንዳንድ ድርጊቶቹ ከላይ ተጠቅሰዋል።
- ለሚሰራው ጸር ህዝብና ኢሰብአዊ ድርጊት አንዳንድ የውጪ መንግስታት ተቃዎሞ እንዳያደርጉበት ለሶሰተኛ ቡድን (ለደላላ) ከፊተኛ ገንዘብ በመክፈል (ሎቢ በማድረግ) አግባብቶ ተቀውሞን ያከሽፋል።
- ላላደረገው ጥሩ ስራ ውሸት ፈጥሮ በመንዛት የማያውቁትን የውጭ አገሮች/ስዎች አጭበርብሮ እንዲደግፉት ወይም እንዳይቃወሙት ያደርጋል።
- አንዳንድ መንግሰታትንም በጥቅማቸው/በድከመታቸው ገብቶ በማሰፋራራት የሚፈልገዉን ድጋፍ እንዲሰጡት ወይም እንዳይቃወሙት ያደርጋል።
- ደሞዝ ከሚከፈላቸው የውጪ አገር የፖለቲካ ባለሞያዎች ጋር አብሮ በቅርብ በመሰራት ለሚፈልገው ኢትዮጵያን የማጥፋትና የግንጠላ አላማ የሚበጅ አገልግሎት ያገኛል።

<u>የተቃዋሚዎች ሁኔታ</u>

- አገር ውሰጥ ለመንቀሳቀስ በመለስ ቡድን ህጋዊነት የተሰጣቸው
    - o የመንግሰት (የቡድኑ) አካል ሆነው የሚሰሩ (ምሳሌ፡ የአቶ የልደቱ፤ የዶ/ር በየነ፤ የዶ/ር መረራ፤ የአቶ ጫሚሶ ወዘት) ፐርቲዎች

      - ከፊሎቹ በብሄር/በጎሳ የተደራጁ ሲሆኑ የቀሩት ህብ-ረብሄ (አገር እቀፍ) ናቸው።
      - ከሞላ ጎደል የመለሰ ቡድን እንደሚፈልገው የሚሰሩ ስለሆነ ተቃዋሚነታቸው አጠራጣሪ ነው።
      - የመልሰ ቡድን ታዛዥ ሆነው ሰለሚቆጠሩ ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር (ማለት፡ ከነሱ ውጪ ከሆኑ) አብሮ የመሰራት ችግር አለባቸው። ሰልሆነም ለሰፊው የኢትዮፐያ ህዝብ ጥቅም የሚያደሩጉ ትግል አነሰተኛ ወይም ባዶ ነው ለማለት ይቻላል።

    - o የመንግሰት (የቡድኑ) አካል ሳይሆኑ የሚንቀሳቀሱ (ምሳሌ፡ የአቶ ሃይሉ፤ የወ/ት ብርቱካን፤ የአቶ ገብሩ) ፓርቲዎች

      - ከፊሎቹ በብሄር/በጎሳ የተደራጁ ሲሆኑ የቀሩት ህብረ-ብሄር እቀፍ ናቸው።
      - እነዚህ ድርጅቶች አሁን ያለውን ህግ/ቀዳዳ በመጠቀም በሰላማዊ ትግል ለዉጥ እናመጣለን ባይ ናቸው።
      - ባደረጃጀት አለመመሳሰል፤ በመጠነኛ የፖሊሲ/የፐሮግራም ልዩነቶች፤ በስልጣን ሽኩቻ ወዘተ የተነሳ ተባብሮ ለአንድ አላማ ለመሰራት ይቸገራሉ።

- አገር ውሰጥ ለመንቀሳቀስ በመለስ ቡድን ህጋዊነት ያልተሰጣቸው

o በጎሳ/በብሄር የተደራጁ ተገንጣዮች

- ምሳሌ፡ የኦሮሞ "ነጻ አውጪ" ድርጅት፤ የኦጋዴን "ነጻ አውጪ" ድርጅት ወዘተ
- የመለሰ ቡድን አይነት አላማ ያላቸው
  - o በኢትዮጵያዊነታቸው የማያምኑ
  - o በኢትዮጵያ ላይ ጥላቻ ያላቸው
  - o ተገንጥለው የራሳቸውን አገር ለመመስረት የሚፈልጉ

o በጎሳ/በብሄር የተደራጁ የመንገንጠል አላማ ግን ያላሳወቁ
- ምሳሌ፡ የአቶ በረሄ የትግራይ ድርጅት
- በኢትዮጵያ አንድነት በማመን በብሄረሰብ መልክ መደራጀትን የተቀበሉ (እንደ ዶ/ር መረራ ድርጅት የመሰለ)

o አገር አቀፍ (ህብረ-ብሄር) የሆኑ

- ምሳሌ፡ ኢህአፓ/ኢህአፓዴ፤ ግንቦት 7፤ ህብረት (የውጪው)፤ መኢሶን፤ ወዘተ
- በኢትዮጵያ የግዛትና የህዝቧ አንድነትና እኩልነት የሚያምኑ
- ህዝብ ያልደገፈውን የመከፋፈልና መገንጠልን አላማና እርምጃ መሚቃወሙ
- በሰልጣን ላይ ያለውን ቡድን በጦር ሃይልም ሆነ በሰላም ለመታገል የተነሱ
- ስልጣን የህዝብ ነው ብለው በማመን በአገሪቷ ህዝባዊ/ዴሞክራሲያዊ መንግስት በማቋቋም ላይ ጽኑ እምነትና ፖሊሲ/ፕሮግራም ያላቸው

<u>የቡድኑ አካል ሳይሆኑ ግን ደጋፊ የሆኑ</u>

- በዚህ የሚጠቃለሉት ይህንን የመስሉ ናቸው

  - በዘር/በጠባብነት የሚያምኑ
  - እንደእነሱ ያልመሰሉትን ሌሎችን ሁሉ በፍራቻና በእውቀት ማነስ የሚጠራጠሩ
  - በግል ጥቅምና ሰልጣን የተገዙ
  - በቡድኑ ፕሮፓጋንዳ የተሸጡ
  - ሳያምኑበት ዳጋፊ እንዲሆኑ የተግደዱ

<u>የቡድኑ አካል ሳይሆኑ ግን ተቃዋሚ ያሆኑ</u>

- በዚህ የሚጠቃለሉት ይህንን የመስሉ ናቸው

  - በአገራቸው አጠቃላይ ሁኔታ ተሰፋ የቆረጡ
  - በተቃዋሚ ድርጅቶች ያልተጠቃለሉ ወይም እምነት የሌላቸው
  - ለሁሉም የአገር ጉዳይ በቂ ግንዛቤ ወይም ግድ የሌላቸው
  - ሳያውቁ ለቡድኑ በመሳሪያነት የሚያገለግሉ

<u>ማጠቃለያና መደረግ ካለባቸው አማራጭ ነገሮች አንዳንዶቹ በጨረፍታ</u>

- የመልሰ ቡድን ኢትዮጵያን አጥፍቶ ትግራይን ለመገንጠል የተነሳና ጠንክሮ የሚሰራ ቡድል ነው
- ቡድኑ ይህንን ካላደረገ ህልውናውን ወይም ያባላቱን መኖር ሰለሚጠራጠር የግድ በዚህ መግፋት አለበት
- ቡድኑ ስራዉን በትጋት ሰለሚያካሂድ፤ በአገሪቱ የሚያመጣው ጥፋት ሊታረም ወይም ሊሰተካከል ከማይቻልበት ደረጃ ሳይዘግይ ሊደርሰ የሚችል ነው፤ ሰለሆነም የተዋውሞ ትግሉ ከጊዜም ጋር ጭምር ነው
- በተመሳሳይ ሁኔታ የተደራጁ ሌሎች ተቃዋሚ የጎሳ ድርጅቶችም ሰልጣን አልያዙም እንጂ አላማቸውና ሰራቸው ተመሳሳይ ነው፡ ሰለሆነውም በምንም መልኩ መደገፍ የለባቸውም

- ኢትዮጵያን ለማጥፋት መስሎ ባይታይም፤ ለፖለቲካ ሰልጣን ተብሎ በጎሳ መደራጀት በምንም መልኩ ጸረ-ዴሞክራሲ ስለሆነ ጎጂና ብሎም አገር አጥፊ ሊሆን የሚችል ነው፤ በመሆኑም ድጋፍ ሊሰጠው አይገባም
- በጎሳ የተሰባሰቡ የድርጅቶች አባላትን ስለአደረጃጀታቸው ጎጂነት በማስተማር፤ ስለሌላ ወገናቸውና ስለአገራቸው ትክክለኛዉን ሁኔታ በማሳወቅ አብረው ለጋራ ጥቅምና ደህንነት የሚሰሩበትን መንገድ መፈለግና ማመቻቸት ይገባል
- ለአገርና ለወገን አሳቢ በመሆን ተቀራራቢ አደረጃጀትና አላማ ያላቸው አገር ውስጥም ሆነ ውጪ ያሉ ድርጅቶች አብረው በይበልጥ የሚሰሩበትን ሁኔታ በአስቸኳይ መፈለግ አለባቸው። ይህንን ላማድረግ

  - ልዩነት ሳያደርጉ ለጋራ ጥቅም መደጋገፍን በይፋ ማሳየት አለባቸው
  - ያለበቂ መረጃ መካሰሰን፤ መሰዳደበን፤ ሃሜትን/ስም ማጥፋትን ማቆም አለባቸው
  - በዴሞክራሲ አሰራር መገዛትንና በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ደግሞ በፍጥነት እርማት የማድረግ ሃላፊነትን መቀበል ይኖርባቸዋል
  - አገርና ህዝብ የጣለባቸውን ዋነኛ ሀላፊነት ሳይሰቱ የሚፈለገውን ግብ ለመምታት በአንድ ላይ ጸንተው መቆየት እንዳለባቸው መቀበል ይኖርባቸዋል

- እያንዳንዱ ለአገርና ለወገን የቆመ (ማለት ልዩነት ሳያደርግ) ሃቀኛ ተቃዋሚ ድርጅት

  - ለይስሙላ ሳይሆን የመለሰ ቡድን የግድ በታቀደ ጊዜ ተነስቶ ኢትዮጵያ ነጻ መውጣት አለባት ሳያወላዳ የጊዜ ገደብ በማድረግ መስራት አለበት
  - ከወቅቱ ጋር የሚሄድ አሰራርን ለመከተል ጥረት ማድረግ ወይም ብቁ መሆን ይኖርበታል
  - ዴሞክራሲያዊ ካልሆነ የአሰራር ጽባይ ፍጹም መራቅ አለበት
  - ሰህተት ሲሰራ ይቅርታ መጠየቅ ወይም በቶሎ ማረም መቻል አለበት
  - ከጥፋቱ ወይም አዲስ የሆነ ነገር ለመማር ዝግጁ መሆን ይኖርበታል
  - አባላትን ወይም ደጋፊዎችን ለመጨመር በትጋት መሰራት አለበትው
  - ለሚያከናውነው ተግባር እንደተጨባጩ ሁኔታ ለኢትዮጥያ ህዝብ ዘገባ መሰጠት ይኖርበታል
  - የውጪ ፖሊሲውን አሻሽሎ ወይም ለውጦ የመለሰ ቡድን ከውጪ የሚያገኘውን ድጋፍ አሰቁሞ ለራሰ ለማድረግ መብቃት። ጥረት ከተደረገ ተጨባጩ ሁኔታ ለዚህ የሚያመች እድል የሚሰጥ ነው።

- አቋም ያልወሰዱ ወይም በፍራቻ የተያዙ ድርጅቶችና ግለሰቦች

  - የመለሰ ቡድን የሚያደርገው ጥፋት ከፍተኛና ጊዜ ሰጪ አለመሆኑን ተገንዝበው አገር አድን አቋምና ድፍረት ሊኖራቸው ይገባል
  - ቡድኑ የሚያደርሰው ጥፋት ገደብ የለሽ ሰለሆነ፤ በማናቸውም ጊዜ በነሱም ላይ ችግሩ በቀጥታ የሚደርሰ ነው፤ የጊዜ ጉዳይ መሆኑን ልምድ በገሃድ ለሁላችንም አሳይቷልና።
  -

- በጥቅም የተገዙ ድርጅቶችና ግለሰቦች

  - የመለሰ ቡድን አገር አጥፊ መሆኑን ተገንዝበው ለጥቅም ሲሉ የሚሰጡትን ድጋፍ ማቆም አለባችው። አገር ከጠፋች በኋላ የተካበተ ሃብትና ንብረት ምን ሊያደርግ ይችላል? አገር ከጠፋች ሁሉም ከንቱ ሊሆን እንደሚችል ከአሁኑ ታውቆ ለአገርና ለወገን የሚበጅ አቋም በአፋጣኝ መውሰድ ብልሀነት ነው።
  - እሰካሁን ባያደርጉትም ቅሉ፤ ህዝብ የሚፈልገዉን ትክክለኛ አቋም ከእንግዲህ ወዲህ እነዚህም የሚከተሉ ከሆነ የመልሰ ቡድን እንደሚያሰፈራራው ሳይሆን፡ ህዝቡ ይቅር እንደሚላቸውና እንደሚያቅፋቸው ጥርጥር የለዉም።

- በቡድኑ ፕሮፓጋንዳ የተታለሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች

  - ትክክለኛውን የአገርና የህዝብ ሁኔታ ለመረዳትና እራሳቸውንም ሊመጣ ከሚችል አደጋ ላማዳን የሌላውን ህዝብና ድርጅት ችግርና እሮሮ ዞር ብለው ለመመልከት በአሁኑ ወቅት መብቃት አለባቸው። ይህ ሲሆን በቡድኑ ፕሮፓጋንዳ የተደፈነውን አእምሮ ሊከፍተው ይችላል።

በኢትዮጵያ የተሻለ አሰተዳደር/መንግሰት ለመመሰረት ይቻላል
ጊዜውም አሁን ነው

www.ethiomedia.com – A site of alternative news and views